# በህቡዕ የመደራጀት ግዴታ

ባለፈው ፅሁፌ *"የዘር ማጥፋት ዝግጅት በኢትዮጵያ"* የሚል ፅሑፍ ፅፌ እንደነበር ይታወሳል ፣ በፅሁፋ ለማሳሰብ እንደሞከርኩት በሐገራችን ኢትዮጵያ አለመታደል ሆኖ የወያኔ የዘረኛ አገዛዝ ባመጣብን ጦስ የተነሳ በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ተቀባይነት የሌለውና የተከለከለ የዘር (የብሄር) አደረጃጀትና በዚሁ የብሄር ቀመር ዜጎችን የማካለል እኩይ ተግባር በመፈፀሙና አሁንም አገራችንን በመምራት ላይ ያለው የኦሮሞ የተረኛችና ጠባቦች ቡድን የወያኔውን አደረጃጀት በመተካት ሆኖም ግን ከወያኔም በከፋ ሁኔታዎችን እያባባሰና እያጋጋለ በመሄዱ ሐገር እንደ ሐገር ትቆማለች ወይ? የሚለውን ጥያቄ ውስጥ ያስገባ አስፈሪና አደገኛ አካሄድ እየሄደ እንደሆነ ባይናችን እያየነው ነው ።

የኦሮሞ ብሄረተኞች ለዘመናት *"አማራ ማለት ኢትዮጵያ ማለት እንደሆነ"* እንዲሁም *"ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ) ማለት አማራ ማለት"* እንደሆነ ለተከታዮቻቸው ሲሰብኩ እንዲሁም አማራ ማለት ጨቋኝና የቅኝ ገዢ አድርጎ በመሳል ምሁሮቻቸው ሳይቀሩ በጣም በሚያሳፍርና በሚያሳዝን ሁኔታ እንዴት ሲያስቱት እንደኖሩ አይተናል ፣ ከብዙ በጥቂቱ ለማስታወስ ያክል ዶክተር ገመቹ መገርሳ የተባሉ ምሁር ተብዬ *"ኦርቶዶክስ መሆን ወይንም ክርስትናን መቀበል ማለት አማራ መሆን ማለት ነው"* በሚል በሚያሳፍር ትንታኔ በሚዲያ ቀርበው የዕውቀታቸው ጥግ እስከምን ድረስ እንደሆነ እራሳቸውን በወረደ ሁኔታ በማጋለጥ መማርና ማወቅን ጭቃ ቀብተው አፈር አልብሰው አሳይተውናል ። https://www.youtube.com/watch?v=4WO4W4cABfs

እንግዲህ እነዚህ የኦሮሞ ምሁራን ተብዬዎች ናቸው ዛሬ በኦሮሚያ ውስጥ የአኖሌ ሃውልት ሽፋን ያለው የጥላቻ የታሪክ መፅሐፍ አሳትመውና አዘጋጅተው ህፃናትን ከልጅነታቸው ጀምሮ በጥላቻ ኮትኩቶ በማሳደግ አማራ ጠል እንዲሆኑና ለዘለዓለሙ የአማራው ጠላት ሆነው መታረቅ እንዳይችሉ ቀርፀው በማሳደግ ላይ እንደሆኑ እንደሆነ ዛሬ የአይን ምስክሮች እየሆንን ነው ። ይህን ሃቅ ለማጣራት የኦሮሞ ክልል የታሪክ ትምህርት የሚሰጡበትን መፅሐፍት መመልከቱ ከበቂ በላይ ምስክር ይሆናል ።

ይህ በጥላቻ የታነፀውና የተገነባው የኅብረተሰብ ክፍል ዛሬ የሐገሪቱን መከላከያ በአንድ ብሄር የበላይነት ማዋቀሩ ሳያንስ ባጓዳኙ በኦሮሚያ ውስጥ ከአንድ ብሄር ብቻ የተውጣጣ ከ150,000 ሺህ በላይ ልዩ ኃይልና ፖሊስ አሰልጥኖ እንዳስመረቀ በመንግሥታዊ ሚዲያዎች ማለትም ተረኛውና በስልጣን ላይ ያለው አመራር አሳይቶናል ።

በተመሳሳይ ሁኔታ የትግሬው ወያኔ እንዲሁ ከአንድ ዘር የተውጣጣ ልዩ ኃይልና ሚሊሺያ አሰልጥኖና ለጦርነት እየተዘጋጀ እንደሆነ ሁላችንም አይተናል ። እዚህ ላይ አንባቢያን እንዲገነዘቡ የምፈልገው እነዚህ ሁለት ፅንፈኛ ቡድኖች በድምር ከ 300,000 ሺ በላይ ልዩ ኃይልና ታጣቂ እንዳላቸው የሚታወቅ ነው ። ታዲያ ይሄ ሁሉ ሽር ጉድ ለምን አስፈለገ? ብሎ እራስን መጠየቅ የግድ ይላል ። ጉዳዩን ስንመረምር ሁለቱም ፅንፈኛ ቡድኖች የዛሬ 40 እና 50 ዓመት በፊት ሲፈጠሩ አፈጣጠራቸው አማራ ጠል እንደሆነና በማኒፌስቷቸውም ላይ አማራን እንደ ጨቋኝና ቅኝ ገዢ አድርገው በሀሰት ትርክት የተደራጁና እስከ አጥንታቸው ድረስ ዘልቆ እስኪገባ ድረስ አማራን አምርረው የሚጠሉ እንደሆኑ ፣ አማራን ድንበሩን በመጋፋት ከሁለቱም ቡድኖች የአማራው መሬቱ እየተዘረፈ እንዳለ ፣ አማራው ከሌለው ብሄር ሁሉ ተገልሎ እራሱን እንዳያደራጅና እንዳይታጠቅ ማድረጋቸው ፣ ዛሬም ብአዴን (አዴፓ) የተባለው የሆነው አሳፋሪ ቡድን በስም አማራን እወክላለሁ ቢልም ሆኖም ግን ፊት ወያኔን ዛሬ ደግሞ ኦዴፓ (ኦነግ) ን አገልጋይ የሆነውን ይባስ ብለው በብልጽግና ተተክቶ በኦሮምኛ ተናጋሪዎች ሊመራው እየተዘጋጀ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ፣ ለዚህም ተጨባጭ ማስረጃ የብልፅግና መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 5 የፓርቲው የስራ ቋንቋዎች በሚለው "ሐ" ላይ እንዲህ ሲል አስቀምጦታል *ሐ) ክልሎችና የአካባቢ ቅርንጫፍ ፓርቲ ፅ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የስራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም አለባቸው* ። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ከማንም የተሰወረ ይሆናል ብዬ አላምንም ። የተጨማሪ ቋንቋን አስፈላጊነት ለምን እንደተካተተ ባለፈው ፅሁፌ ላይ ስላብራራሁት እዚህ ላይ አልደግመውም ።

ወደተነሳሁበት ርዕስ ስመለስ ለምን የህቡዕ ድርጅት አስፈለገ ይህስ አደረጃጀት ለማን? የሚለውን ለመዳሰስ እሞክራለሁ ። ከላይ እንደተገለጸው አማራው በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ብሄረሰቦች ማለት ባይቻልም ባብዛኛው ዘንድ ግን አማራውን ጨቋኝና ቅኝ ገዢ ተደርጎ የተሳለው የሃሰት ትርክት ቀላል አይደለም ፣ በተለይ በወያኔ ትግሬዎችና በሁሉም ኦነጋውያን ዘንድ አማራውን ቢቻል ከምድረገፅ ለማጥፋት ባይቻል ግን ቁጥሩን በእጅጉ በመቀነስና አማራው የሚገኝበትን ስፍራዎች ሁሉ በአንድ በኩል በኦሮምኛ ተናጋሪ በሌላው ወገን ደግሞ በትግሪኛ ተናጋሪ ወሮ ወሰኑንም ወደራሳቸው በማካለል የአማራውን ቁጥር እዚህ ግባ ከማይባል አድርሶ አንገቱን ደፍቶና የነዚህ ጠባቡች ተገዥ ሆኖ እንዲኖር ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ እያስተዋልን ነው ።

ይህንንም እኩይ አላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ቀን ከሌት እየለፉበትና እየሰሩበት ይገኛል ። ለዚህም ምስክሩ አንድ ሐገር ፣ እንደ ሐገር ከሚያስፈልገው በላይ ሰራዊት በአማራ ጠሎቹ በየክልላቸው እያሰለጠኑና እያዘጋጁ ባሉበት ወቅት አማራው ግን አይደለም ሰራዊት ማሰልጠን ግለሰቦች እንኳን ሁኔታው አሳስቧቸው "ፋኖና" "የጎበዝ" አለቃ በሚል ተደራጅተው እራሳቸውንና ወገናቸውን ከአይቀሬ ጥቃት ለመታደግ የሚያደርጉትን መሰባሰብና መደራጀት በሚያደርጉበት ወቅት የአማራው ተወካይ ብአዴን (አዴፓ) ዛሬ ደግሞ ብልፅግና የተባለው የባንዳዎች ስብስብ በኦሮሞና በወያኔ

የሚደርስበት በደልና ጥቃት ሳያንሰው የአማራው ጥቅም አስጠባቂ ወይንም ደጀን ነን በሚሉ ሆድ አደሮች ሽፍቶች እየተባሉ እየተሳደዱ እንደሆነ ሰሞኑን እየሰማን ያለው የወቅቱ አሳዛኝና አስገራሚ ክስተት ሆኗል ።

እነዚህ ፋኖ ፣ የጎበዝ አለቃ በሚል የተሰባሰቡትም ሆነ ሌሎች መሰል ስብስቦች ካሉ ወደ አንድ ስብስብ መምጣቱ ጠቀሜታው ለሁሉም ብቻ ሳይሆን ትግሉንም ይበልጥ ሊያሳልጥና ሊያግዝ እንደሚችል በማመን ወደ አንድነት መምጣቱ አጠያያቂ አይሆንም ። በአንፃሩም አንድ የሆነ የትግል መርሆ እንዲኖረውና የእዝ ሰንሰለት መዋቅር ለመዘርጋት ሁኔታዎች የተመቻቹ ስለሚያደርግ በእጅጉ ሊታሰብበትና ሊሰራበት ይገባል ።

አማራው ለኢትዮጵያ አንድነትና ለአብሮነት ሲል ብዙ ቢታገስና ቢችልም ትዕግስቱና መቻሉ ይባስ ጠላቶቹ እንዲጠናከሩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበረከተ እንጂ አስተዋይነቱ ከግንዛቤ ገብቶለት ለጥያቄው መልስ እንዲያገኝ አልተደረገም ። ይልቁንም ከገዛ አብራኩ በወጡ ሆድ አደሮች ለወገኑ መከታ ለመሆን የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ቢቻል ለማፈራረስ ካልተቻለም እድገቱን ለመግታት “በአማራ አነጎችና” “በአማራ ወያኔዎች” የሚደርስበት መሳደድ የሆድ አደሮቹን ይሁዳነት ጥርት አርጎ አሳይቶናል ። አማራው ካብራኩ የወጡት ጥቂት ሆዳደሮችም የጠላት በትር ሆነው በባንዳነት እየሰሩ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ስላስመሰከሩ አማራው የትግሉን ዘዴ ቀይሮ መደራጀትና መታጠቅ እንደሚኖርበት ለነገ ይደር የማይባል አንደብጋቢ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል ።

ከታሪክ በመማር አማራው የህቡዕ አደረጃጀት መስርቶ ትግሉን ማጠናከር ይኖርበታል ፣ ይሄ የጎልውና ፣ የመኖር ወይም ያለመኖር ትግል ስለሆነ የዲሲፒሊንና የሚስጥር አያያዝን ከቀደሙ የኢሐፓ አደረጃጀትና ሚስጥራዊነት በመማር የትግል ስልት ለመንደፍ አዳጋች አይሆንም ። ዛሬ ቴክኖሎጂውም አጋዥ መሆኑ አደረጃጀቱን የበለጠ በሰለጠ ሁኔታ እንዲቀላጠፍ እንደሚረዳው ምንም አያጠራጥርም ። አደረጃጀቱ የዕዝ ሰንሰለት እንዲኖረው በማድረግ እንደቀደመው በቀበሌ ፣ በወረዳ ፣ በዞን ወዘተ እያለ እስከ ማዕከላዊ አመራር ድረስ መስርቶ ቡድኖቹ ቢበዛ ከ 5 እንዳይበልጡ በማድረግ አንድ ከበላይ የሰንሰለቱ ጋር አገናኝ በመወከል ፣ በመርህና በአላማ ፣ በአንድ ወጥ አንድ አይነት አቋምና ግብ እንዲኖረውና እንዲይዝ ከማድረግ ባሻገር በድርጅቱ መዋቅር ውስጥ ማን ምን እንደሆነና ከነማን ጋር እንደሚሰራና እንደሚገናኝ ማወቅ እንደማይኖርበትና አስፈላጊም መሆኑን በመተማመን ፣ በማስተማር ጠንካራና አይበገሬ የሆነ ሕዝባዊ ደጀን መመስረት ይቻላል ። አስፈላጊነቱም ወቅቱን የጠበቀ ስለሆነ አፅንዖት ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል ።

ማንም ቢሆን አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የድርጅቱን አባላት የስራ ድርሻና የግንኙነቱን ሰንሰለት ማወቅ አይኖርበትም ፣ ይህ አይነት የአሰራር ዘዴ አንዱን ለመጥቀም ሌላውን ለመጉዳት ሳይሆን በሆነ አጋጣሚ ከድርጅቱ መዋቅር አንድ ግለሰብ በጠላት እጅ ቢወድቅ ሊያውቅ የሚችለው በጣም የተወሰነ ሊሆን ስለሚችል ድርጅቱን በቀላሉ እንዳይመታና መዋቅሩ እንዳይፈርስ የሚረዳ ስለሆነ ጠቀሜታው ለድርጅቱ ህልውና ዋስትና ብቻም ሳይሆን ለሚደረገውም ትግል ፍሬያማነት ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ስለሚታመንበት ነው ።

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌሎች ድርጅቱን በዲሲፕሊን ፣ በሚስጥራዊነትና በፅናት ሊያንፁ ይችላሉ የተባሉ የተጠኑና የተፈተኑ የአደረጃጀት ዘዴዎችን እንደአስፈላጊነቱ በማከልና በመጠቀም ወደር የማይገኝለት የታለመለትን ዓላማ ከግብ የሚያደርስ ፣ ባሸናፊነት ሊወጣ የሚችል ሕዝባዊ ኃይል ማፍራት ይቻላል ። የጊዜያዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት በህቡዕ የመደራጀቱ ሁኔታ ግዴታ እንጂ ውዴታ ብቻ እንዳልሆነ አምኖ አማራው ከፊቱ የተጋረጡበትን አሜኬላዎች ደምስሶ በድል አድራጊነት ሊወጣ የሚያስችለው አንዱና ብቸኛው አማራጭ መሆኑን ተቀብሎ ወደስራና ተግባር መሰማራት የግድ ይላል ።

ማሳሰቢያ :- ይህንን ፅሁፍ በማዘጋጅበት ወቅ የአማርው ብልፅግና ፓርቲ የተባለው የኦነግ ተላላኪ በጎንደር በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ፋኖንና የጎበዝ አለቃን በከባድ መሳሪያ ጭምር እየደበደበ እንደሆነ ተዘግቧል ። ኦነግ ሸኔ የተባለው የጠባቦች ቡድን በተለያዩ ከተሞች ሽብር እየነዛና ግለሰቦችን እየገደለ ፣ ተማሪዎችን እያገተ ለአመታት ፀረ ሕዝብ ተግባር እየፈፀመ ምንም ያልተደረገ አማራው ግን ገና ለገና ተሰባሰበ ተብሎ ገና አንገቱን ቀና ሊያደርግ ሲሞክር በከባድ መሳሪያ ሳይቀር መምታት መጀመሩ ከዚህ በፊት *“የእንቅልፋሞችና የወኔ ቢሶች አመራር”* በሚለው ፅሁፌ የገለፅኩትንም ሆነ አሁንም በዚህ ፅሁፍ የገለፅኩትን ይበልጥ የሚያጠናክር ሆኖ አግኝቼዋለሁ ።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ

ታዛቢው

March 20, 2020